# ይድረስ ለታማኝ በየነ

ውድ ታማኝ በየነ ይችን ደብዳቤ ስፅፍልህ የት እንተዋወቃለን ብለህ ግራ እንደማይገባህ ተስፋ አለኝ። ምክንያቱም አንተ እኔን ባታውቀኝም እኔ ግን አንተን ታማኝ የኢትዮጵያ ልጅ ነህና አፌን ሞልቼ አውቅሀለሁ ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም። ምንም እንኳ አድራሻህን ባላውቀውም ደብደቤዬ ሚስጥር አዘል ስላልሆነ ከተለጠፈበት ድህረ ገፅ ማንበብ እንደምትችል በመተማመን ነው።

ለአንተ ብዙዎች የቁርጥ ቀን ልጅ ብለው ለሚያምኑብህ ሰው ደብዳቤ ለመፃፍ የተገደድኩበት ዋናው ምክንያት ምንም እንኳን እኔ የየትኛውም የፓለቲካ ድርጅት አባል ባልሆንም፤ ሌት ከቀን የብዙዎቻችን ሰቆቃ የሆነውን የሀገራችንን ጉዳይ በተመለከተ እኔም እንደግለሰብ የሀገሬን ጉዳይ የወገኔን ስቃይ ጆሮ ዳባ ልበስ ብዬ መተው የማልችል፤ የሀገር አንድነት፤ የወገን ደህንነት የሚያሳስበኝ ኢትዮጵያዊ ሴት በመሆኔ፤ በተለይም አንተ ታማኝ በየነ በሀገርህና በሰንደቅአላማህ ላይ አትደራደርም ብየ የማምንብህ ሰው የምትሄድበት መንገድ ትክክል አይደለም ብየ ሳስብ ከመጠቆም የሚገታኝ ነገር በማጣቴ ነው።

''አገሬ ኢትዮጵያ በታማኝ ልጅሽ
ከፍ ብሎ ታዬ ሰንደቅአላማሽ''

ተብሎ የተዘፈነልህ ውድ ታማኝ፤ አሁን ደብዳቤውን ከመፃፌ በፊት ደረጃ ደገፉ ያንጎራጎረልህን ሙዚቃ እያዳመጥኩ እኔም ስንኞቹ ውስጥ ያሉትን የአንተነትህ መግለጫ ስለምጋራ በተለይም ከፍ አድርገህ እንድታውለበልባት የተመረጥከው የቁርጥ ቀን የኢትዮጵያ ልጅ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በአንተ ድጋፍም ጭምር ሰንደቅ አላማችን ከፍ ብላ ኮርታ ሳይሆን ከአጥፊዎቿ ከኦነግና ከሌሎች መሰል ነፃ አውጪ አርማ ጋር ተደበላልቆ መቆሙን በማየቴ የቁጭት ለቅሶ እንዳነባሁ አልደብቅህም '' የሴት ነገር '' ብለህ ስሜቴን በእምባ መግለፄን እንዳታጣጥለው ግን አደራዬ የጠበቀ ነው።

''የጨነቀው እርጉዝ ያገባል፤ ስትወልድበት ገደል ይገባል'' የሚሉት አይነት ካልሆነ በቀር የሀገር አንድነት የሚሰበከው አሁን ግንቦት 7 ወይም ዶር ብርሀኑ በያዘው አይነት እንዳልሆነ የሁላችንም ልቦና ያውቀዋል። በመጀመሪያ ኦነግ እና የኦሮሞ ህዝብ በአንድ ተፈርጆ ኦነግን ካልያዝን ኢትዮጵያን አንድ ማድረግ አንችልም የሚለው የዶ/ር ብርሀኑ ዲስኩር ከውነት የራቀና በጥናት ያልተዳሰሰ አደገኛ አካሄድ ነው ብዬ አምናለሁ።

እውነት ለመናገር በኢትዮጵያ ውስጥ ጭቆና የነበረው የዘር ሳይሆን በማግኘትና በማጣት ላይ የተመሰረተ፤ ያለው የሌለውን ተጭኖ ይገዛ እንደነበረ እናንተም በዘመኑ አጠራር ከአማራ ክልል የመጣችሁት የምታውቁት ይመስለኛል። እኔም በአቅሜ ሁለት ሰዎች በፈረስ ላይ ሆነው ሲተላለፉ የባላባት ስሜት ያላቸው ባለፈረስ፤ የማያስተዳድሩትን፤ በምንም መልኩ ቀጥታ ግንኙነት ያልነበረውን ሌላ አማራ ባለፈረስ ቀድሞ ከፈረስ ወርዶ እጅ ባለመንሳቱ ጉዳዩን እንደ ድፍረት ቆጥረውት ቤታቸው አስጠርተው አክብሮ ሲሄድ ሰውየውን በአሽከር ያስገረፉትን ሰው በደርግ ጊዜ መገራረፍ ካበቃ በኋላ በአካል አግኝቻቸው ታሪኩን ከአስገራፊው የቅርብ ሰዎች ቅሬታቸውን ጭምር ሰምቻለሁ። እስኪ ይህ ተገራፊ አማራ ቁራሽ እንጀራ የማይጥልለት ሰው ምንም ሳይበድለው ሲያስገርፈው ምን እንደሚሰማው በአይነ ህሊናህ አስበው! የተገራፊው ልጆች ምን እየተሰማቸው አድገው ይሆን? ቤተዘምዱስ ምን ተሰምቶት ይሆን?

ሌላው ምሳሌዩ ደግሞ በወሎ ክ/ሀገር የኦሮሞ ባላባት ሴትወይዘሮች ለጤና ተብሎ ቅንድቡ የገጠመ ወንድ ልጅ ተፈልጎ በልጁ ደም ይታጠቡ ነበር። በዚህ መንገድ ልጆች

በየጊዜው ይጠፉና እንደወጡ ይቀራሉ። ታዲያ አንድ ልጁ እንደወጣ የውሀ ሽታ ሆኖ የቀረበት አባት ልጁ የት እንደወደቀ ስለወቀ ሲያለቅስ

"ባልሽ ማመድ አሊ አንች ማን አለብሽ
በየትኛው ዳኛ አቤት ልበልብሽ"

ብሎ አልቅሶ እርሙን አወጣ። እንግዲህ ወ/ሮ ማናለብሽ የኦሮሞዋ እመቤት ያረዱት የአማራውን ልጅ መሆኑ ነው። እንደውም የኦሮሞ ወይዘሮች ሲሞቱ የሴት አገልጋይም ከነነፍሷ አብራ ትቀበር ነበር ይባላል። እኔ እነዚህን ምሳሌዎች መጥቀሴ ችግሩን ለማባባስ ሳይሆን እያንዳንዱ ባላባት ተብዬ ሀብታም እርህራሄ በጎደለው መንገድ ድሀ ወገኑን የቅርብ ቤተሰቡን ሳይቀር ሲያንገላታ መኖሩ ሁላችንም የምናውቀው አንዱና እውነተኛ ያለፈ ታሪካችን መሆኑን ለመጠቆም ነው። ለዚህም በአማራውም አካባቢ ቢሆን የበላይና የበታች እንዴት በመጨካከን እንደኖረ የአዲስ አለማየሁን ፍቅር እስከ መቃብር መፀሀፍ እንደ ዋቤ መጥቀስ ይቻላል። ነገር ግን ሁሉንም ነገር በአንድ ዘር መፈረጁ ወይም በዘር ላይ ያነጣጠረ በደል አስመስሎ ማቅረቡ ለሻቢያ አባላትና ነፃ ወጣ ለተባለው የኤርትራ ህዝብም አልጠቀመም፤ ወያኔም ነፃ አውጭ ነኝ በሎ መጥቶ የሚያደርሰው ግፍና በደል እየታየ ነውና ቢታሰብበት ጥሩ ነው። ለዚያውስ ደርግ መጥቶ መሬት ለአራሹ ብሎ መሬት ለገበሬው ሰጥቶ መልካም አስተዳደር ባለመኖሩ ብቻ ተመልሰን በወያኔ እጅ መውደቃችን ተረስቶ ነው? የመቸውን ቁስል ነው አሁን የምናከው?

በአነጋገርም ቢሆን ሰለጠንኩ ያለ የከተማ ልጅ ነኝ ተብየ ለመግባባት አንደበት ሲከፈት የሚያፌዙት ዘር መርጠው አማርኛ የመጀመሪያ ቋንቋው ያልሆነውን ኦሮሞ፤ ጉራጌ፤ ትግሬ ወዘተ ብቻ ሳይሆን ተናጋሪው አፉን የፈታው በአማርኛ ቢሆንም እንኳ እንደነሱ አይነት የድምፅ ቅላፄ ከሌለው በጎንደሬው በወሎዬው ወዘተ ሲሳለቁ እንደኖሩና አሁንም በዚያው የስተት መንገድ እንደቀጠሉ የሚስተዋል ነው። የዚህ አይነቱን ወገን የማሸማቀቅ አባዜ የምንዋጋው ደግሞ በዘር በመደራጀት ወይም ጥላቻን በላያችን ላይ በማንገስ ሳይሆን ብዙው ጥፋት ባለማወቅ ባለማስተዋል እንደሆነ ተረድተን በዚያ መንገድ ሰው የሚያሳቅቀው ግላስብ ወይም ግሩፕ በዙ ያላገናዘበ መሆኑንና አነጋገሩ ሰው የሚያስቀይምና አፀያፊ መሆኑን እንዲረዳ በማድረግ ሲሆን፤ የሚፌዝበትም ሰው የጎደለው ነገር ስላለ ሳይሆን፤ የአስተሳሰብ ድክመት ባለባቸው ወይም ብዙ ቀልድ የሚወዱ ሰዎች ማስቀየማቸውን ባለማስተዋል የሚፈፅሙት መሆኑን አውቆ ለትችቱ ትኩረት እንዳይሰጥ በማድረግና በሚዲያ ጭምር በመወያየትና በማስተማር ነው።

ነገር ግን ኦነግ በስደት ለልጆቹ ብሎም ለልጅ ልጆቹ የዘራውን መርዝ ድንገት ይቀይራል የሚባለው ነገር ተጨፈኑ እናሙኛችሁ ካልሆነ በቀር የኦነግ መሪዎች ከአንደበታቸው አልወጣም። እንደውም ተወካዮቹ አስረግጠው የነገሩን በአቋማቸው መፅናታቸውን ብሎም ሌላው የህብረተሰብ ክፍልም እንደ ግንቦት 7 እውቅና እንዲሰጣቸው ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሚያወቀው ከሆነ ደግሞ ኦነግ ለአጭር ጊዜም ቢሆን በአስተዳደር በቆየበት ዘመን ከወያኔ ጋር ተመሳጥሮ ኤርትራን ያስገነጠለና የዋህንን እያነሳሳ በመላው ኢትዬጵያ ያሉትን አማርኛ ተናጋሪዎች ህፃንና ነፍሰጡር ሳይቀር በገደል እንዲወረወሩና እንዲታረዱ ያደረገ በዘር የተለከፈ አጥፊ ድርጅት ነው።

ዶ/ር ብርሀኑ ነጋን በተመለከተ፡- በውነቱ ዶ/ር ብርሀኑ ለቅንጅትና ህብረት የድጋፍ ገንዘብ ለማሰባሰብ ከዶር መራራ ጉዲና ጋር እኔ በምኖርበት አገር መጥቶ በተለሳለሰ አነጋገሩ ወያኔን ኢህአድግ በሉ እያለ ፍቅር ሲሰብክ በወያኔ ላይ ያለኝን ጥላቻ እንዲቀንስ አስተዋፅዖ አድርጓል። ለዚህም ለጊዜው ያመሰገንኩት ቢሆንም አሁን አሁን ግን ሳስበው እንደጠቀመኝ እርግጠኛ አይደለሁም። ምክንያቱም ቅንጅት ሲፈራርስ ማዳን የሚያስችል አቅም ባይኖረኝም ጥፋት እየታዘብኩ ውስጤ እያረረ ከዳር ከቆሙት አንዷ በመሆን እንደታዛቢ ሆኘ ያየሁት ወኔ በማጣቴ እንደሆነ እገምታለሁ።

ግንቦት 7 በውስጡ ውድ ኢትዮጵያውያን በቅን ልብ ያጀቡት ኢትዮጵያዊ ድርጅት ነው ብለን ብናስብ እንኳ መሪው ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ግን የዘሩ መርዝ ሰለባ እንዳልሆነ ማረጋገጥ አይቻልም።

የኸንን ለማለት የሚያስደፍረኝ ብዙ ነጥቦች ቢኖሩኝም በአገሩ ጉዳይ አንገቱን ይሰጣል እንጅ አይደራደርም የሚባል ሰው እንዳልሆነ እንኳን ሌላው ኢትዮጵያዊ እሱም ቢጠየቅ የሚክድ አይመስለኝም። ለዚህም ነው የሰለጠነ ፖለቲካ እያለ በአገሩ ላይ ላለመደራደር ቁርጥ አቋም ባለው ኢትዮጵያዊ ወኔ ላይ ውሀ እየቸለሰ ወኔውን በማብረድ ለእሱ አላማ ተከታይ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚጥረው። ሰውየው በኢትዮጵያ አንድነት ላይ በፅናት የቆመ ላለመሆኑ አለፍ አልፍ ብየ መረጃ መጥቀስ ያስፈልገኛል።

በወጣትነት ዘመኑ ኢህአፓ የነበረው ብርሀኑ ነጋ ዘልቆ በድርጅት አባልነቱ አለመቀጠሉ ስረመሰረቱ ምክንያቱን ስለማላውቅ ልተወውና አንተ ታማኝ እንደግለሰብ የወያኔ አገዛዝ አጥፊ መሆኑን ተረድተህ በየአደባባዩ ድምፅህን በምታሰማበት ጊዜ እሱ ኤርትራ ስትገነጠል ጭምር ምንም ሳይቆጨው ውስኪ ሲራጭ በፎቶ ግራፍ ጭምር ያየነው ሰው ነው። ያኔ ባጠፋው ለመክሰስ ሳይሆን ሁሉንም ቀስተዳመና ሆኖ ለቅንጅት ውህደት ደፋ ቀና ሲል ያየው ህዝብ ጥርጣሬውን ወደጎን አድርጎ አምኖ ተቀብሎት ነበር። እሱ ግን ህዝቡ ነፃነት ወይም ሞት ብሎ በወኔ በተነሳበት ጊዜ ከማንም የቅንጅት አመራር ሳይማከር በደረቅ ሌሊት ከዶ/ር በየነ ጴጥሮስ ጋር በቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ብሎ የተመከረበት አድማ እንዳይደረግ ብቻውን ወስኖ ከቅንጅት እሳቤ ውጭ ባስተላለፈው መልክት አመፁን አደናቀፈ።

በእርግጥ ለቅንጅት መፍረስ መንስዔው አንድ ብርሀኑ ነጋ ብቻ ነው ባልልም ከፍተኛውን ሚና ለመጫወቱ በወቅቱ የነፃነት ተስፋችን በቅንጅት ላይ የተመረኮዘ ስለነበር ሁኔታውን በቅርብ ተከታትያለሁና ምን ምን እንደተከናወነ ዛሬ እንደሆነ ሁሉ ወለል ብሎ ይታየኛል።

በነገራችን ላይ እኔ ዶ/ር ብርሀኑንም ሆነ ሌሎቹን የቅንጅት አባላት የማውቀው አንተን እንደማውቀው የሀገሬን ጉዳይ ስላነገቡ እንጅ የተለየ ነገር የለኝም። እንደውም ዶ/ር ብርሀኑ በወያኔ እስር ቤት በነበረ ጊዜ እጁ በሰንሰለት ታሰረ የሚለው ዜና ሲደርስን በግለሰብ ደረጃ በተለይ ያሰብኩለት የተጨነኩለት ቢፈታ በኢኤፍዲ ምክንያት የተከፋፈለውን ህዝብ አንድ ያደርጋል የሚል አጉል ተስፋ በእሱ ላይ ጥየ ነበር። ይህንንም ያደረኩት ከንግግሩ ለሰላም፤ ለአገርና ለወገን የቆመ መሆኑን እንደወረደ በመውሰዴና ቃሉን በማመኔ ነበር። አሁን ግን በተደጋጋሚ የሚሰራውን ስታዘብ "አውቆ የተደበቀ ቢጠሩት አቤት አይልም" እንዲሉ አውቆ ለሚሰራው ተው ማለት ጉንጭ ማልፋት ነውና እያዘንኩ ተቃውሞየን አሰማለሁ።

ቀደም ብሎ የወያኔ ባለስልጣናት ጋርም ቢሆን በየጊዜው እየተገናኘ በስልክም እያወራ የቅንጅትንና የኢትዮጵያን ህዝብ እጣ ፈንታ ወደፈለገው አቅጣጫ ያሽከረከረው ለመሆኑ ከአንደበቱ የተደመጠ ሲሆን፤ ዲሞክራሲ ዲሞክራሲ እያለ የሚጮኸው ዶ/ር ብርሀኑ ቅንጅት ከተመሰረተ በኋላ አባል ያደረጋቸው እነወ/ሪት ብርቱካን መዴቅሳ የቅንጅት አባል ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የአመራር ቦታ እንዲይዙ በማድረግ ለረዥም ጊዜ ህዝብ በማደራጀት የታወቁት እነ ልደቱ አያሌው በሁኔታው ባለመስማማት አፈንግጠው ሲወጡ በህብረተሰቡ እንዲጠሉ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል። ይህን ስል አቶ ልደቱ ለብዙሀን ድምፅ አለመገዛቱ ትክክል ነው ለማለት ሳይሆን አቶ ልደቱ ማጥፋቱ ዶ/ር ብርሀኑን ከተጠያቂነት አያድነዉምና ላስገነዝብ የምወደው ነገር አሁንስ የሚካሄደው ነገር ከበፊቱ ልምዳችን ጋር ሊስተዋል አይገባውም ወይ ነው።

ከሁሉም የሚገርመው ደግሞ ተመልሶ አገሩ ገብቶ እንደማይታገል ልቡ እያወቀ፤ ሙያ በልብ ነው ብሎ ከሰው በፊት ፈርጥጦ ከአገር የወጣው ታጋይ፤ የቅንጅት አድራጊ ፈጣሪ

EthioLion.Com

መስሎ የአንድነት ሀይሉ ፍርክስክሱ እስኪወጣ ድረስ በመላው አሜሪካ እየዞረ በሚችለው ሁሉ የታገለና ገንዘብ ያሰባሰበ መሆኑ ነው።

ዶ/ር ብርሀኑ ቅንጅት ከፈራረሰ በኋላም ንግግሩ አደገኛ ሲሆን እንደምሳሌ "መለስ የሚባል የትግሬ ዲክታተር አውርደ ኃይሉ የሚባል የአማራ ዲክታተር" እያለ በመርዛማ ዘረኛ አነጋገር የዘር አባዜ የያዛቸውን መሰሎቹን ቁስል በማከክ የአንድነት ትግሉን አዳክሟል። ለዚያውም አቶ ኃይሉ ሻውል ግማሽ ኦሮሞ ግማሽ አማራ መሆናቸውን እያወቀ እሳቸውን እንደ ግለሰብ ዘር ሳይጠቅስ መኮንን ሲችል! ዘርም ከጠራ ዘራቸው በትክክል መጥራት ሲገባው ሆነ ብሎ አጉል ተወዳጅነትን ለማትረፍና አማራ ወያኔና ሻቢያ ጥርስ ያስነከሱበት ሳያንስ እሱም በሌለ ነገር ተመርኩዞ በአንድነት ሀይሉ ላይ ተረማምዷል። አሁንማ ጭራሽ እየለየለት ሲመጣ ወገኖቻችን ደማቸውን ባፈሰሱለት በማይጨው ጦርነትና በሀገራቸው ደህንነትና በመልካም አስተዳደራቸው ታሪክ የመሰከረላቸውን አፄ ምኒሊክን ሳይቀር ከዘረኞች አብሮ በየአደባባዩ ሲጎነታትላቸው ይደመጣል።

የሰላምና የነፃነት ሀዋርያ የነበረው ዶ/ር ሰንበት ብሎ ከአሁን በኋላ የማንንም ልጅ ወደ ጦርነት አንልክም፤ ለውጥ የሚመጣው በሰላማዊ ትግል ብቻ ነውና የመሳሰሉትን ባለበት አፉ ወያኔን በሰላም ትግል ማውረድ አይቻልምና በጦር እዋጋለሁ ሲል ተደመጠ። ለዚህም የሚያስፈልገው የተወሰኑ ሰዎች 500 ዶላር መዋጮ ነው ቶሎ ክፍያውን ያጠናቀቀ ታጋይ የአርበኝነት ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል ሁሉም ነገር በስድስት ወር ይጠናቀቃል ተባለና አርበኝነት በገንዘብ ተተምኖ ለለጋሾቹ የአርበኝነቱ ምስክር ወረቀት ታደላቸው። በመቀጠልም ኤ ኤፍ ዲ ብሎ ቀርቦ የአንደነቱን ሀይል ሲከፋፍል የነበረውን ጎጠኛ ቡድን እንደገና ስሙን ቀይሮ በማጠናከር ከገንጣዮች ጋር ዝምድናውን ያጣድፈው ገባ። እንግዲህ ''ወደሽ ከተደፋሽ ቢረግጡሽ አይከፋሽ'' እንዲሉ እንደ ዶ/ር ብርሀኑ አይነት ብልጣብልጦች ቅንነት በጎደለው መንገድ በህልውናችን ላይ ሲደራደሩ፤ መሞከሪያ ሲያደርጉን እስከ መቸ አጉል ትህትና ይዞን አብረን አጥፍተን ልንጠፋ እንዘጋጃለን?

እኔ የሚያሳስበኝ በተለይ የአንድነት ሀይሉ ባልተጠናከረበት ሁኔታ ገንጣይ ጋር መዶለቱ እ.ኤ.አ. በ1991ዓ.ም በለንደኑ ስብሰባ እነ ኮሎኔል ጎሹ ወልዴና መሰሎቻቸው ምን ሊደርስ እንደሚችል እየተናገሩ፤ በሀገር ቤትም ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ያለሰሚ እንደጮሁ ለህልፈተ ህይወት የበቁ ሲሆን ጊዜው የገንጣይና የአስገንጣይ ስለነበር ድምፃቸው/ጩኸታቸው ተውጦ አገራችን በወያኔና ኦነግ ተመርታ ኤርትራ ከእናት አገሩዋ ተገነጠለች፤ ኢትዮጵያም ባህር በር አልባ መሆኑዋ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። ለዚህም ዲሞክራሲ በሌለበት አገር ኤርትራን ለማስገንጠል የተጠቀሙት የምርጫ ድምፅ " ነፃነት ወይም ባርነት " እንደሆነ ሁሉ፤ ወያኔ ህብረተሰቡ 90% እንደሚቃወመው እየታወቀ 99.6 % እንዳሸነፈው ሁሉ አሁንም የሀገራችን እጣ ፋንታ በዚሀ መንገድ እንዳይቋጭ ታማኝ ወንድሜን በጥብቅ ላሳስብህ እወዳለሁ።

የሀገራችን ችግርና የመፍትሄ ሀሳብ :- አሁን የአገራችን ችግር ነው ብየ የማስበው ብዙዎችም የሚስማሙበት የመልካም አስተዳደር ዕጦት መሆኑን ነው። በዚህም ምክንያት ህፃናት በትርፍ ይሸጣሉ፤ ወጣት እህቶቻችን በየአረብ አገሩ በተለያየ መንገድ ይሰቃያሉ፤ ከፎቅ ይወረወራሉ፤ በአረብ ወንድ በግድ ይደፈራሉ፤ ባሏን የፈራች ቀናተኛ ሴት ሰለባ ሆነው በአሲድ ይቃጠላሉ፤ ስማቸውን ስለሚቀይሩና ማንነታቸው ስለማይታወቅ እናቶቻቸው፤ ቤተሰቦቻቸው እርም የማውጣት እድል የላቸውም። ወንድሞቻችን በሰሀራ በረሀ ወድቀው ይቀራሉ፤ እነሱም በአረብ ግብረሰዶም ፈፃሚወች ይደፈራሉ በየ ጠረፉ ድንበር ሲያቋርጡ በጠረፍ ጠባቂ ወታደር እየተመቱ የሚወድቁትንና በየባህሩ ወድቀው የሚቀሩትን ቤት ይቁጠረው። ገበሬው መሬቱ ለአረብ፤ ህንድ፤ ቻይና፤ ፓኪስታን ወዘተ ባለፀጋወች ስለሚሸጥ ከቀየው ይፈናቀላል። ኑሮ በመወደዱ ምክንያት የከተማው ሰው ፆም አዳሪ በመሆን ስለተጎዳ ታሞ አይነሳም፤ እንደቅጠል ይረግፋል። በአገሪቱ ርሀቡ ከእኛ ጆሮ አልፎ አለምን የሚያሳስብበት ደረጃ ላይ ደርሷል። የማን ዘር ነው የሚባል ጥያቄ ለችግሩ

መፍትሄ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም የዚህ ሁሉ መከራ ገፈት ቀማሽ ሁሉንም ዘር ያካተተው የኢትዮጵያ ህዝብ ነውና።

"የአህያ ባል ከጅብ አያስጥልም" እንዲሉ የግንቦት 7 ቅስቀሳ የነ ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው አዳማቂነት የኢትዮጵያ ህዝብ ከምንም የማይቆጥረውን ኦነግ እውቅና ከመስጠት ባለፈ በአንድነትና በነፃነት ስም ሰው በሰውነቱ በሚደርስበት በደል ተነስቶ ለነፃነት ከመታገል እንዲቆጠብ፤ ተበዳይ በበዳይ ላይ ከማተኮር ይልቅ በጅምላ የመፈረጅ ስሜት እንዲኖረው ከማድረግ በተጨማሪም አጥፊ ወንጀለኛ በሰራው ወንጀል እንዳይጠየቅ የሚሸጎጥበት የወንጀለኛ ግለሰቦች ጎራ ማድረግ፤ አለያም አንዱ ወገን አንዱን የእኔ ወይም እኛ እንዳይል፤ እኛና እነሱ እያልን የጎሪጥ እንድንተያይ የሚያደርግ ስለሆነ ለተደራረበ የማያባራ መከራ ይጥለናል እንጅ ወደ መፍትሄ አይወስደንምና ሁላችንም ከፀፀት እንድንድን በቅን ልቦና ሆነን በሀገራችንና በህዝባችን ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጥቅምና ጉዳቱ አስበን በአንድነታችን ላይ ከመደራደር እንቆጠብ እላለሁ።

የአገራችን ውድቀት የህዝቡ ችግር፤ ሞቱ፤ ስደቱና ርሀቡ በዘር ፓለቲካ የሚቋጭ ችግር አይደለም። ከላይ የዘረዘርኩት ችግርም ሆነ ወያኔ ሆነ ብሎ የሚፈፅመው የአገዛዝ ጫና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የዳሰሰ ማለትም የአማራ፤ የኦሮሞ፤ የከንባታ፤ የሀድያ፤ የወላይታ፤ የጉራጌ፤ የአፋር የአገው የሱማሌ የአኙዋክ ወዘተ ህዝብ በአጠቃላይ ኢትዮጵያዊዉ ስለሆነ፤ መፍትሄ የሚያገኘው በአንድነቱ ሀይል ህብረትና ጥንካሬ ነውና ቅድሚያና ትኩረትህ ወደ አንድነቱ ቢሆን አገርህን የበለጠ መጥቀም ብቻ ሳይሆን አንተን በማየት ብቻ ዘረኛ የሚከተለው ኢትዮጵያዊ የቁርጥ ቀን ልጅ ከስህተት ይድናል።

ወንድሜ ታማኝ ብዙ የመስራት አቅም እንዳለህ አረዳለሁ። አባባሌ ሁሉ አንተን አጥፊ አድርጌ ለመኮነን እየዳዳኝ ሳይሆን አንተን የማከብርህን ታማኝ በየነ ለአገር ይጠቅማል ብለህ እንጅ የአገርህን ጉዳይ ልብህ እያወቀ አደጋ ላይ ትጥላለህ ብየ ስለማላምን፤ ምንአልባት እኔና መሰሎቸ የታየን አደጋ አንተ ካልታየህ ነገሩን በቅን ልቦና እንድታየው በትህትና አሳስብሀለሁ።

ለዚህም ግንቦት 7 የአንድነቱን ሀይል ወደጎን ጥሎ አገር እገነባለሁ ብሎ ከዘረኛ ጋር ደፋ ቀና ሲል ተባባሪ ከመሆን ይልቅ፤ ባይሆን የአንድነቱን ሀይል በማሰባሰብ የአገር ፍቅር ስሜት ሌት ከቀን የሚያንገበግበውን ስደተኛ ኢትዮጵያዊ በአንድነት በማስተባበር እያንዳንዱ በስደት ያለ ኢትዮጵያዊ በነፍስ ወከፍ ቢያንስ $1,1 ቢያዋጣ በስደት በየአረብ አገሩና በየበርሀው መሰቃየትና መሞትን የመረጠውን ኢትዬጵያዊ ወገን ጠግነን በስደት መሞትን የውርደት ሞት መሆኑን አምኖ በውድ አገራችን ላይ ባንድነትና በክብር ለነፃነት ታግለን ከሞትንም ሞታችን ለሀገራችን በሀገራችን እንዲሆን የኢትዮጵያዊነት መንፈስ መልሶ በልባችን እንዲያንሰራራ ማድረጉ አማራጭ የሌለው መፍትሄ ነው ብዬ አምናለሁ። እንግዲህ ሰው ያለውን ከወረወረ ፈሪ አይባልም እንደሚባለው እኔም የተሰማኝን ለማከብርህና ለማደንቅህ የአገሬ ልጅ አሳስቤለሁ ጉዳዩን ትኩረት ሰጥተህ እንደምታስብበበት ተስፋ አለኝ።

አገሬ ከስዊድን
ሐምሌ 24 2011

EthioLion.Com